በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር
THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
MINISTRY OF FOREIGN AFFAIRS
የፕሬስ መግለጫ
PRESS RELEASE

## የቀድሞው የደቡብ አፍሪካ ፕሬዝዳንት ኔልሰን ማንዴላን ህልፈት ምክንያት በማድረግ የወጣ መግለጫ

የቀድሞው የደቡብ አፍሪካ ፕሬዝዳንት ኔልሰን ማንዴላን ህልፈት በተመለከተ የኢፌዴሪ መንግስት የተሰማውን ጥልቅ ሃዘን ለአገሪቱ ህዝብና መንግስት የገለፀ ሲሆን፣ ለቤተሰቦቻቸውም መጽናናትን ተመኝቷል፡፡

ፕሬዝዳንት ማንዴላ በደቡብ አፍሪካ የአፓርታይድን ስርዓት ለማስወገድ የተደረገውን ከፍተኛ ትግል የመሩ የነፃነት ታጋይ ከመሆናቸው ባሻገር፣ መላው አፍሪካ ከጭቆናና ከውጭ ኃይሎች አገዛዝ ነፃ እንዲወጣ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደረጉ ታላቅ መሪ ነበሩ፡፡ ፕሬዝዳንት ማንዴላ ለሰብዓዊ መብት መከበር፣ ለዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ፣ እንዲሁም በሕዝቦች መካከል ሰላማዊ ግንኙነቶችን በማንባት ያበረከቱት አስተዋጽኦ ከትውልድ አገራቸው ደቡብ አፍሪካ አልፎ በመላው አፍሪካ እንዲሁም በዓለምአቀፍ ደረጃ እውቅና አስገኝቶላቸዋል፡፡

ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለማርያም ደሳለኝም የወቅቱ የአፍሪካ ህብረት ሊቀመንበር እንደመሆናቸው ለአገሪቱ መንግስት ባስተላለፉት የሃዘን መግለጫ መልዕክት በፕሬዝዳንት ማንዴልና በኢትዮጵያ መካከል ያለው ትውውቅና ወዳጅነት ረጅም ዘመናትን ያስቆጠረ መሆኑን አስታውሰው፣ አገራችን ፕሬዝዳንቱ ለታገሉለት የሕዝቦች ነፃነትና የዲሞክራሲ ስርዓት ግንባታ ያላትን ታማኝነት አረጋግጠዋል፡፡

**የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር**
**ቃል አቀባይ ጽ/ቤት**
**ህዳር 30 ቀን 2006 ዓ.ም.**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር
THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
MINISTRY OF FOREIGN AFFAIRS
የፕሬስ መግለጫ
PRESS RELEASE

## **Statement on the Death of Former**
## **South African President Nelson Mandela**

The People and Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia received with profound sorrow the news of the passing away of former South African President Nelson Mandela – a visionary leader, who dedicated his life for the achievement of freedom and justice for his people. His legacy will live on for generations to come.

President Mandela did not only lead his country's struggle against Apartheid but has also been the torch bearer in the quest for Africa's freedom. He inspired generations of world leaders to stand for justice, human dignity and freedom across the globe.

H.E. Mr. Hailemariam Dessalegn, Prime Minister of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and Chairperson of the African Union expressed most profound sympathies and sincere condolences to the family of President Mandela as well as to the People and the Government of the Republic of South Africa. In his message, Prime Minister Hailemariam stressed the special place President Mandela has in the hearts of all Ethiopians. He recalled the brief period that the former freedom fighter spent in Ethiopia during his exile in the 1960s and expressed Ethiopia's commitment to uphold his messages of selflessness, humility and dedication to the struggle for freedom and human dignity that this towering African icon taught humanity.

Indeed, President Mandela leaves behind a great vision from which all of us Africans should draw inspiration. The Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia will continue to value the principles of democracy, freedom, justice, tolerance and reconciliation for which President Mandela dedicated his life.

**Ministry of Foreign Affairs**
**Office of the Spokesperson**
**09 December 2013**
**Addis Ababa**